


# ስለ አባ ሰንጋ
# የሚያስረዳ መመሪያ

## አባ ሰንጋ - ተላላፊ በሽታ


የአዳዲስ እና እንስሳ ወለድ ተላላፊ በሽታዎች ብሔራዊ ማዕከል

U.S. Department of
Health and Human Services
Centers for Disease
Control and Prevention



ይህ ሰነድ የተፃፈዉበአማርኛ ሲሆን፤ የእንግሊዝኛ ቅጂዉበ
http://www.cdc.gov/anthrax/basics/index.html ሊገኝ ይችላል፡፡

# ስለአባ ሰንጋ የሚያስረዳ መመርያ

## ማውጫ


መሰረታዊ መረጃ ..... 2
አባ ሰንጋ ምንድን ነዉ? ..... 2
እንሰሳት በአባ ሰንጋ እንዴት ይጠቃሉ? ..... 2
እንሰሳት በአባ ሰንጋ እንዴት ይበከላሉ? ..... 2
አባ ሰንጋ የት ይገኛል? ..... 2
የአባ ሰንጋ አይነቶች ..... 3
የቆዳ አባ ሰንጋ ..... 3
የእስትንፋስ አባ ሰንጋ ..... 3
የሆድዕቃ አባ ሰንጋ ..... 3
የመርፌ አባ ሰንጋ ..... 3
ሰዎች እንዴት እንደሚበከሉ ..... 4
ከተበከሉ እንስሳቶች ወይም የእንስሳት ዉጤቶች ጋር በመስራት ..... 4
የተመረዙ እንስሳትን ጥሬ ወይም ያልበሰለ ስጋ መመገብ ..... 4
ሄሮይን መወጋት ..... 4
አባ ሰንጋ ተዛማች ነዉን? ..... 4
የአባ ሰንጋ ምልክቶች ..... 5
የቆዳ አባ ሰንጋ ምልክቶች፥ ..... 5
የእስትንፋስ አባ ሰንጋ ምልክቶች፥ ..... 5
የሆድዕቃ አባ ሰንጋ ምልክቶች፥ ..... 5
የመርፌ አባ ሰንጋ ምልክቶች፥ ..... 5
አባ ሰንጋን መመርመር ..... 6
የስነህይወት ሽብር ..... 7
አባ ሰንጋ እንደ ጦር መሳርያነት ለምን ጥቅም ላይ ይዉላል? ..... 7
አባ ሰንጋ ምን ያህል አደገኛ ነዉ? ..... 7
የአባ ሰንጋ ጥቃት ምን ሊመስል ይችላል? ..... 7

# ማኅረታዊ ሚረጃ

## አባ ሰንጋ ምንድን ነ ው?

አባሰንጋ ማለት ባሲለስ አንትራኪስ በሚበለዉቀጥ ያለ ቅርፅ ባለዉ፣ ግራምፖዝቲቭበሆነ ዉባክቴሪያ የሚፈጠር ከባድተላላፊ በሽታነ ው። አባ ሰንጋ በተፈጥሮ አፈር ወስጥ ሲገኝ፤ በአብዛኛዉበመላውአለም የ ሚገኙየ ቤት እና የ ዱር እንሰሳትን ያጠቃል። ምንምእንኳን በአሜሪካ ወስጥ አናሳ ቢሆንም፤ ሰዎች ከተበከለ የእንሰሳ ተዋዕፆ ጋር ወይምከተበከለ እንሰሳ ጋር ንኪኪ ከፈጠሩ በአባ ሰንጋ ሊታመሙ ይችላሉ። ከአባ ሰንጋ ጋር የ ተደረገ ንኪኪ ለሰወም ሆነ እንስሳን ለከፋ ህመምይዳርጋል።

አባ ሰንጋ ተዛማች **አይደለም፤** ማለትምእንደ ጉንፋን ወይምሳል በትንፋሽ ሊተላለፍ አይችልም።




## እንሰሳት በአባ ሰንጋ እንዴት ይጠቃሉ?

እንደ በሬ፣ በግ፣ ፍየል፣ ድኩላ እና አጋዘን ያሉ የ ዱር እና የ ቤት እንሰሳት በተበከለ አፈር ወስጥ ያለን የ አትክልት ዘር ወይምወሃ በሚግጡ ጊዜ ወይምከአየ ር ወደ ወስጥ በሚሁነ ፍሱበት ጊዜ ሊበከሉ ይችላሉ። የ ቤት እንሰሳት በአባ ሰንጋ በተበከሉባቸዉአካባቢዎች፤ በተደጋጋሚየ ተደረገ ክትባት ተዛማችነ ቱን ሊከላከል ይችላል።

## እንሰሳት በአባ ሰንጋ እንዴት ይበከላሉ?

የ አባ ሰንጋ ዘር ወደ ሰዉነ ት ወስጥ ሲገ ባ ሰዎች ይበከላሉ። የ አባ ሰንጋ ዘሮች ወደ ሰዉነ ት ወስጥ ሲገ ቡ፤ «ሊነ ቃቁ»ይችላሉ። ንቁ ሲሆኑ ፤ ባክቴርያዉሊባዛ፣ በሰዉነ ት ወስጥ ሊሰራጩ፣ መርዞችን ሊያመ ጭእና ከባድ ህመምሊያስከትል ይችላሉ።

ሰዎች የ ዘሩን ብናኝ ከአየ ር ወደ ወስጥ ሲተነ ፍሱ፣ በዘሩ የ ተበከለ ምግብ ሲበሉ ወይምወሃ ሲጠጡ፤ ወይምዘሩ በተቆረጠየ ሰዉነ ት ክፍል ወይምየ ቆዳ ቁስል ወስጥ ሲገ ባ ሊፈጠር ይችላል። በአሜሪካ ወስጥ ሰዎች በአባ ሰንጋ ማበከል ያልተለመደ ነ ው።

አንዳንድእንቅስቃሴዎች የ አንድን ሰዉየ ማበከል ዕድልን ሊጨምረዉይችላል። ለበለጠመረጃ፤ ሰዎች እንዴት እንደሚበከሉ የ ሚለዉን ይመልከቱ።

## አባ ሰንጋ የ ት ይገ ኛል?

አባ ሰንጋ በመካከለኛና በደቡብአሜሪካ የ እርሻ አካባቢዎች፣ ከሰሃራ በረሃ በታች ባሉየ አፍሪካ ሃገ ራት፣ በመካከለኛና ደቡብምስራቅ እስያ፣ ደቡብና ምስራቅ አወሮፓና በካሪብያን አካባቢዎች ወስጥ የ ሚገ ኝ ነ ው።

አባ ሰንጋ በአሜሪካ ወስጥ ያልተለመደ ቢሆንም፤ ነ ገ ር ግን በዱር እና እንደ በሬ ወይምአጋዘን ባሉበቤት የ ጋጣእንሰሳት ላይ እንደ ተዛማች ወረርሺኝ ይከሰታሉ። አባ ሰንጋ በታዳጊ ሃገ ራት እና ለእንሰሳት በተደጋጋሚየ አባ ሰንጋ መከላከያ ክትባት የ ሚሰጡየ ሕዝብ ፕሮግራሞች በሌሉባቸዉሃገ ራት በአብዛኛዉየ ተለመደ ነ ው።
በአሜሪካ፤ ከዚህ ቀደምአባ ሰንጋ የ ተጠቁ እንስሶች ባሉባቸዉአካባቢዎች አመታዊ የ እንስሳት ክትባት ይመከራል።

# የ አባ ሰን ጋ አይነ ቶች

በአንድ ግለሰብ ዉስጥ የ ሚፈጠረዉ የ ህመም አይነ ት አባ ሰን ጋ በሰዉ ነ ት ዉስጥ እንደገ ባበት ሁኔ ታ ይወሰናል። በዋነ ኛነ ት፤ አባ ሰን ጋ ወደ ሰዉ ነ ት ዉስጥ በቆዳ፣ በሳንባ ወይም በሆድዕ ቃ በኩል ይገ ባል። ሁሉም የ አባ ሰን ጋ አይነ ቶች በሂደት ወደ ሰዉ ነ ት ሁሉ ሊሰራጩ በፀረ-ባክቴሪያ መድሃኒ ት ካልታከመ ሞት ሊያስከትል ይችላል።



## የ ቆዳ አባ ሰን ጋ

የ አባሰን ጋ ዘር በአብዛኛዉ ወደ ቆዳ ዉስጥ በቀዳዳ ወይም በቁስል ሲገ ባ፤ አንድ ግለሰብ የ ቆዳ አባ ሰን ጋ ሊያዳብር ይችላል። ይህም የ ሚሆነ ው፤ አንድ ሰዉ የ ተበከለ እንስሳ ወይም እንደ ጥጥ፣ ጨርቅና ፀጉር የ ሆኑ የ ተበከለ እንስሳ ዉጤቶችን ሲይዙ ነ ው። የ ቆዳ አባ ሰን ጋ በጭንቅላት፣ አንገ ት፣ የ ዉስጥ ክንዶችና እጆች ላይ የ ተለመደ ነ ው። በተበከለዉ አካባቢ ያሉ ሕዋሳትንና ቆዳን ይጎ ዳል።

የ ቆዳ አባ ሰን ጋ ከአባ ሰን ጋ አይነ ቶች በአብዛኛዉ የ ተለመደዉ ሲሆን ፤ ከሌሎቹ ይልቅ አደጋዉ አነ ስተኛ ነ ው። መሚዚ ዙ የ ሚጀምረዉ ለባክቴሪያ ዉ ተጋላጭ ከሆነ ከ 1 እስከ 7 ቀን በኋላ ነ ው። የ ህክምና ክትትል ካልተደረገ ፤ በቆዳ አባ ሰን ጋ ከታመመሰዎች ዉስጥ 20% ለሞት ይዳረጋሉ። ሆኖም ግን ፤ ተገ ቢዉ የ ሕክምና ክትትል ከተደረገ ፤ በአብዛኛዉ ሁሉም የ ቆዳ አባ ሰን ጋ ታካሚዎች በሕይወት ይቆያሉ።



## የ እስትንፋስ አባ ሰን ጋ

አንድ ግለሰብ የ አባ ሰን ጋ ብናኝ ዘሮችን በእስትንፋስ ወደ ዉስጥ ሲስብ፤ የ እስትንፋስ አባ ሰን ጋ ሊያዳብር ይችላል። በጥጥ ፋብሪካ፣ በእንሰሳት የ እርድ ቤቶችና የ ቆዳ ማምረቻ ፋብሪካ ዉስጥ የ ሚሰሩ ሰዎች ከተበከሉ እንሰሳት ወይም ከተበከሉ የ እንሰሳት ዉጤቶች የ ዘር ብናኙን በእስትንፋስ ወደ ዉስጥ ሊያስገ ቡ ይችላሉ። የ እስትንፋስ አባ ሰን ጋ ወደ መላ ሰዉ ነ ት ከመሰራጨቱ በፊት በቀዳሚነ ት በደረት አካባቢ ባሉ የ መተንፈሻ አካላት ይጀምርና በመጨረሻም ሲከፋ ከባድ የ አተነ ፋፈስ ችግር እና መንቀጥቀጥ ያመጣል።


የ እስትንፋስ አባ ሰን ጋ በጣም አገ ደኛ የ አባ ሰን ጋ አይነ ት እንደሆነ ይታሰባል። መሚዚ ዙ የ ሚጀረታው፤ ለባክቴሪያ ዉ ተጋላጭ ከሆኑ በሳምንት ዉስጥ ሲሆን ፤ እስከ 2 ወራት ጊዜ ሊወስድ ይችላል። የ ህክምና ክትትል ካልተደረገ ፤ በ እስትንፋስ አባ ሰን ጋ ከታመመሰዎች ዉስጥ 10 - 15% የ ሚደርሱት ብቻ በሕይወት ይቆያሉ። ሆኖም ግን ፤ ጥብቅ በሆነ የ ሕክምና ክትትል ወደ 55% የ ሚደርሱ ታካሚዎች በሕይወት ይቆያሉ።



## የ ሆድዕ ቃ አባ ሰን ጋ

አንድ ግለሰብ ጥሬ ወይም ያልበሰለ ሥጋ በአባ ሰን ጋ ከተበከለ እንስሳ ሲመ ገብ፤ የ ሆድዕ ቃ አባ ሰን ጋ ሊያዳብር ይችላል። የ አባ ሰን ጋ ዘሮች አንዴ ወደ ዉስጥ ከገ ቡ፤ የ ላይኛዉን የ ሆድዕ ቃ ክፍሎች (ጉሮሮ እና የ መተንፈሻ ቧንቧ)፣ ሆድ እና አንጀቶችን ይጎ ዳሉ።

የ ሆድዕ ቃ አባ ሰን ጋ በ አሜሪካ ዉስጥ የ ተገ ዘገ በዉ በጣም አናሳ ጊዜ ነ ው። መሚዚ ዙ የ ሚጀምረዉ ለባክቴሪያ ዉ ተጋላጭ ከሆኑ ከ 1 እስከ 7 ቀን በኋላ ነ ው። የ ህክምና ክትትል ካልተደረገ ፤ በሆድዕ ቃ አባ ሰን ጋ ከታመመሰዎች ዉስጥ ከግማሽ በላይ ይሞታሉ። ሆኖም ግን በተገ ቢዉ የ ሕክምና ክትትል፤ ከታካሚዎች ዉስጥ 60% በሕይወት ይቆያሉ።



## የ መርፌ አባ ሰን ጋ

በቅርቡ፤ በሰሜን አዉሮፓ የ ሄሮይን ሱስ የ ሚያስይዝ መድሃኒ ት በመርፌ በሚወስዱ ተጠቃሚዎች ዉስጥ ሌላ የ አባ ሰን ጋ አይነ ት ተገ ኝቷል። የ ዚህ አይነ ቱ የ አባ ሰን ጋ ማበከል በአሜሪካ አልተዘገ በም።

ምልክቶቹ ከቆዳ የ አባ ሰን ጋ አይነ ት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ፤ ነ ገ ር ግን ሱስ የ ሚያስይዝ መድሃኒ ቱ በመርፌ በሚወጋበት ጊዜ ከቆዳ ስር ወይም በጡንቻ ዉስጥ ቁስል ሊፈጥር ይችላል። የ መርፌ አባ ሰን ጋ ወደ ሙሉ ሰዉ ነ ት በአፋጣኝ ሊሰራጭና ለይቶ ለማከም አዳጋች ሊሆን ይችላል። ሌሎች ብዙ የ ባክቴሪያ አይነ ቶች የ ቆዳ እና የ መወጋት ቁስሎችን ሲያስከትሉ ስለሚችሉ፤ ሱስ የ ሚያስይዝ መድሃኒ ት ተጠቃሚዉ የ ቆዳ ወይም የ ተወጋበት አካባቢ መሚዚ ዝ ካለዉ ግለሰቡ አባ ሰን ጋ አለበት ማለት አይደለም።

# ሰዎች እንዴት እንደሚበከሉ

የአባ ሰንጋ ዘር ወደ ሰዉነት ወስጥ ሲገባ ሰዎች ይበከላሉ። ይህ ሲሆን፤ ዘሮቹ ሊነቃቁና የአባ ሰንጋ ባክቴሪያ ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚያም ባክቴርያዉ ሊባዛ፣ በሰዉነት ወስጥ ሊሰራጭ፣ መርዞችን ሊያመነጭ እና ከባድ ሕመም ሊያስከትል ይችላል። ሰዎች የዘሩን ብናኝ ከአየር ወደ ወስጥ ሲተነፍሱ፣ በዘሩ የተበከለ ምግብ ሲበሉ ወይም ዉሃ ሲጠጡ፤ ወይም ዘሩ በተቆረጠ የሰዉነት ክፍል ወይም የቆዳ ቁስል ወስጥ ሲገባ ሊፈጠር ይችላል።

## ከተበከሉ እንስሳቶች ወይም የእንስሳት ወጤቶች ጋር በማስራት

በአባ ሰንጋ የታመሙ ብዙ ሰዎች የተጋለጡት ከተበከሉ እንስሳቶች ወይም እንደ ጥጥ፤ ቆዳ ወይም ፀጉር ካሉ የእንስሳት ወጤቶች ጋር በማስራት ነዉ።

የእስትንፋስ አባ ሰንጋ አንድ ግለሰብ በኢንዱስትሪ ሂደት ወስጥ ያሉ እንደ ጥጥ፣ ቆዳ ወይም ፀጉር ባሉ በተበከሉ ዕቃዎች አማካይነት ዘሮቹን በእስትንፋስ ወደ ወስጥ ሲስብ ሊከሰቱ ይችላሉ።

የቆዳ አባ ሰንጋ የተበከሉ የእንሰሳት ወጤቶችን የያዙ ሰራተኞች የዘሩ ብናኝ በተቆረጠ ወይም በቆሰለ ቆዳ ወስጥ ሲገባ ሊከሰት ይችላል።

## የተሚዙ እንስሳትን ጥሬ ወይም ያልበሰለ ስጋ መማብ

የተሚዙ እንስሳትን ጥሬ ወይ ያልበሰለ ስጋ መማብ የሆድዕቃ አባ ሰንጋ ሊያስከትል ይችላል። ይህ ምበአብዛኛዉ የአባ ሰንጋ ክትባት ለእርባታ እንስሳት በቋሚነት በማይሰጥበት እና ለምግብ የሚዉሉ እንስሳት ከእርድ በፊት በማይመረመሩባቸዉ ሃገራት ሊከሰት ይችላል።

በአሜሪካ ወስጥ የሆድዕቃ አባ ሰንጋ በአናሳ ሚሊኩ ተዘግቧል። ምክንያቱም ከዚህ ቀደም በአባ ሰንጋ የተያዙ እንስሳት በነባሩባቸዉ አካባቢዎች አማታዊ የእንስሳት ክትባት ስለሚደረግ እና ሁሉም ለምግብ የሚዉሉ እንስሳት በእርድ ጊዜ ጤናማ ታቸዉ ስለሚረጋገጥ ነዉ።

## ሄሮይን መወጋት

አዲስ የተገኘዉ የአባ ሰንጋ አይነት የመርፌ አባ ሰንጋ ነዉ። የዚህ አይነቱ አባ ሰንጋ በሰሜን አወሮፓ ሄሮይን በሚወጉ ሰዎች ላይ ታይቷል። እስካሁን ድረስ፤ ምንም አይነት የመርፌ አባ ሰንጋ አልተዘገበም።

## አባ ሰንጋ ተዛማች ነዉን?

**አይደለም። አባ ሰንጋ እንደ ጉንፋን ወይም ሳል በትንፋሽ ከሌላ ሰዉ አይተላለፍም።** ወስን በሆኑ ጊዜያት፤ ከቆዳ የሚወጡ ፈሳሾች ማከል የተነሳ ከሰዉ ወደ-ሰዉ የተላለፈ የቆዳ አባ ሰንጋ ተዘግቧል።

# የአባ ሰንጋ ምልክቶች

የአባ ሰንጋ ምልክቶች ለመታየት አንደ መሚዙ አይነት ከ 1 ቀን እስከ 2 ወራት ሊወስድ ይችላል። ሁሉም የአባ ሰንጋ አይነቶች የሕክምና ክትትል ካላገኙ ወደ ሰዉነት ሁሉ ሊሰራጩእና ከባድ ህመም ሲከፋም ሞት የሚከተል አቅም አላቸው።

## የቆዳ አባ ሰንጋ ምልክቶች፥



- የሚያሳክኩ ትናንሽ እብጠቶች ወይም ወሃ መቋጠር
- ቁስሉ አካባቢ ያለ እብጠት
- ከትናንሽ እብጠቶች ወይም ዉሃ መቋጠር በኋላ ከሚፈጠር ጥቁር ምልክት ጋር ሕመም የሌለዉ የቆዳ ቁስል (አልሰር)፣ አብዛኛዉን ጊዜ ቁስሉ በፊት፣ በአንገት፣ በክንድ ወይም በእጆች ላይ ይሆናል

## የእስትንፋስ አባ ሰንጋ ምልክቶች፥



- ትኩሳት እና ብርድ ብርድ ስሜት
- የደረት አለመመቸት
- የትንፋሽ መቆራረጥ
- ግራ መጋባት ወይም መፍዘዝ
- ሳል
- ማቅለሽለሽ፣ ትዉከት፣ ወይም የሆድ ሕመሞች
- ራስ ምታት
- ላብ (አብዛኛዉን ጊዜ በላብ ማጥመቅ)
- ከባድ የድካም ስሜት
- የሰዉነት ህመሞች

## የሆድዕቃ አባ ሰንጋ ምልክቶች፥

- ትኩሳት እና ብርድ ብርድ ስሜት
- የአንገት ወይም የአንገት እጢዎች እብጠት
- የጉሮሮ ቁስል
- በመዋጥ ግዜ የሚኖር ሕመም
- የድምፅ መጎርነን
- ማቅለሽለሽ እና ትዉከት፤ በተለይም ደም ማስታወክ
- ተቅማጥ ወይም የደም ተቅማጥ
- ራስ ምታት
- የፊት መቅላት (ፍምፊት) እና የአይን መቅላት
- የሆድ ሕመም
- ራስን መሳት
- የሆድ እብጠት (የሆድዕቃ)

## የመርፌ አባ ሰንጋ ምልክቶች፥

- ትኩሳት እና ብርድ ብርድ ስሜት
- መድሀኒት በተወጋበት አካባቢ የሚታዩ የሚያሳክኩ ትናንሽ እብጠቶች ወይም ዉሃ መቋጠሮች
- ከእብጠቶች ወይም ዉሃ ከመቋጠር በኋላ መሃከል ላይ የሚታይ ጥቁር ምልክት ሕመም ከሌለዉ የቆዳ ቁስል ጋር
- ቁስሉ አካባቢ ያለ እብጠት
- መድሀኒት የተወጋበት ቆዳ ስር ወይም ጡንቻ አካባቢ ያለ መመርቀዝ

**ሊታወሱ የሚገቡ ነገሮች**

የመርፌ አባ ሰንጋ ምልክቶች ከቆዳ አባ ሰንጋ ምልክቶች ጋር ተመሳሳይ ቢሆኑም፤ የመርፌ አባ ሰንጋ ግን ከቆዳ አባ ሰንጋ ይልቅ በሰዉነት ወስጥ በፍጥነት ሊሰራጭእና ለይቶ ለማከም ሊያዳግት ይችላል። የቆዳ እና የመወጋት ቁስሎችን መድሀኒት ከመወጋት ጋር የተያያዙ በመሆናቸዉ የመድሀኒት ተጠቃሚዉ የቆዳ ወይም የተወጋበት አካባቢ መመሚዝ ካለዉ ግለሰቡ አባ ሰንጋ አለበት ማለት አይደለም። ሐኪሞች አባ ሰንጋን ለመመርመር እንዲረዳቸዉ የሲዲሲ ማምሪያና የማሕደር ትንተናዎች ይገኛሉ

# አባ ሰንጋን መመርመር



በአሜሪካ ያሉ ሐኪሞች የአባ ሰንጋ ህመምተኛ የሚያዩት በጣምአናሳ ነ ው። ሐኪሞች አባ ሰንጋን ለመመርመር እንዲረዳቸው፣ ታካሚዎች እንዴት ለበሽታዉእደተጋለጡታሪካቸዉን ለማወቅ፣ እናምአስፈላጊዉን የምርመራ ናሙናዎች ለማዘዝ፤ የሲዲሲ መምሪያ እና የሜሕደር ትንተናዎች ይገኛሉ።

የአባ ሰንጋ በትንፋሽ ወደ ወስጥ ማሳብ ከተጠረጠረ፣ በእስትንፋስ አባ ሰንጋ ታማሚወስጥ የሚታዩ የራጂ ግኝቶች፤ የደረት ክፋይ ማስፋት ወይምበሳምባ አካባቢ ወሃ መቋጠር እንዳለበት የደረት ራጅ ወይምሲቲ ስካን ማረጋገጥ ይችላል።

የአባ ሰንጋ ምርመራን ማረጋገጫብቸኛ መንገዶች እነ ዚህ ናቸው፥

- በደምወስጥ ያለን የፀረ-ባክቴሪያዎች ወይምየመርዝ ማጠን ማስካት
- በናሙና ◦ደምወስጥ ባሲለስ አንትራኪስ ን በቀጥታ መመርመር
    - የቆዳ ቁስልን ማፅዳት
    - የጀርባ አጥንት ፈሳሽ
    - የመተንፈሻ ፈሳሽ ማመንጨት

ታካሚዉለሕክምና ፀረ-ባክቴሪያ ከመዉሰዱበፊት ናሙናዎች መወሰድ አለባቸው።

# የስነ ህይወት ሽብር

ሌላ የአባ ሰንጋ ጥቃት ይከሰት እንደሆነ ወይምመቼ እንደሆነ አናወቅም። ሆኖምግን፤ የመንግስት ድርጅቶች በሃገር ወስጥ ካሉ ከጤና ክፍል ሃላፊዎች ጋር ስለ ሌላ የአባ ሰንጋ ጥቃት ለማቀድ እና ለማዘጋጀት ለአመታት ሰርተዋል። በአሜሪካ እንዲህ አይነት ድንገተኛ ሁኔታ በፈጠር፤ ሲዲሲ እና ሌሎች የመንግስት ድርጅቶች ከሀገር ወስጥ እና ከክልል አጋሮች ጋር በቅርበት በማስራት ተገቢዉን ምላሽ ያስተባብራሉ።

## አባ ሰንጋ እንደ ጦር ማርያነት ለምን ጥቅምላይ ይወላል?

የባዮ-ሽብር ጥቃት ቢፈጠር፤ ጥቅምላይ ሊወል ከሚቻል የስነ ህይወት ማርያ አንዱ አባ ሰንጋ የሚፈጠርበት ባክቴሪያ፤ ባሲለስ አንትራኪስ ነው። የስነ ህይወት ንጥረነገሮች ሰዎችን፣ እንስሳትን ወይምሰብሎችን ማስመም ወይምመግደል የሚቹሉ ተዋህሲያን ናቸው፡ በዋነኝነት ጥቅምላይ ሊወል ከሚቻል ንጥረነገር አንዱ አባ ሰንጋ ነው፤ ምክንያቱም፥

- የአባ ሰንጋ የዘር ብናኝ በተፈጥሮ ወስጥ በቀላሉ የሚገኝ ስለሆነ ፤ በላቦራቶሪ ወስጥ ሊሚረት እና በአካባቢ ወስጥ ለረዥምጊዜ ሊቆይ ይችላል።
- አባ ሰንጋ በዝግታና ማንምሳያወቅ ማለቀቅ ስለሚቻል፤ አይነተኛ ማርያ ሊሆን ይችላል። በአይን የማይታዩ ደቃቅ ብናኞች በዱቄቶች ወስጥ፣ በሚረጩ በምግብና በወሃ ወስጥ ሊገቡ ይችላሉ። በጣምትንሽ ከመሆናቸዉየተነሳ፤ በአይን ሊታዩ፣ ሊሸት ወይምሊቀመሱ አይችሉም።
- አባ ሰንጋ ከዚህ ቀደምእንደ ጦር ማሪያነት ጥቅምላይ ወሏል።

አባ ሰንጋ ለአንድ ምዕተ ዓመት ያህል በአለምዙርያ እንደ ጦር ማርያነት ጥቅምላይ ወሏል። በ 2001 ዓ.ም፤ በተቀነባበረ ሜልኩ አባ ሰንጋ ብናኞች በደብዳቤ ወስጥ ተቀምጠዉበአሜሪካ የፓስታ አገልግሎት በኩል ይላኩ ነበር። 12 የፖስታ ሰራተኞችን ጨምሮ ሃያ ሁለት ሰዎች በአባ ሰንጋ ተይዘዋል፤ ከእነዚህም 22 ሰዎች ወስጥ አምስቱ ሞተዋል።

## አባ ሰንጋ ምን ያህል አደገኛ ነው?

እነዚህን ስነ ህይወታዊ አነሣሾች እና መርዞች ሆን ብሎ አላግባብ ማጠቀም ብዙ ጉዳት ወይምአስደንጋጭየ ኢኮኖሚ ተፅዕኖ፣ አሳሳቢ ማረተልማት፣ ወይምየሕዝብ መተማመን ለሕዝብ ጤና እና ደሕንነት የሚጋርጠዉ ጥብቅ ስጋት በሚድረሳቸው የተነሳ የተሚረጡየ ንጥረነገሮች ስብስብና መርዞች እንደ ደረጃ 1 ተሰይመዋል። ባሲለስ አንትራኪስ ደረጃ 1 አነሣሽ ነው።

ቢ. አንትራኪስ የተሚረጠ አነሣሽ ነው። የ ባ. አንትራኪስ ባለቤትነት፣ አጠቃቀም ወይምዝወወር በ ሲዲሴሴ የሕዝብ ጤንነት ማካላከያና መቆጣጠሪያ ቢሮ በሚገኘዉ በየተሚረጡ አነሣሾች እና መርዞች ክፍል (ዲሴኤቲ) ቁጥጥር ስር ነው።

## የአባ ሰንጋ ጥቃት ምን ሊመስል ይችላል?




የአባ ሰንጋ ጥቃት ብዙ ቅርፆችን ሊይዝ ይችላል። ለምሳሌ፤ በ 2001 እንደተደረገዉ የአባ ሰንጋ ዘር ብናኞች ደብዳቤ ወስጥ ተቀምጦ በሜልዕክት ሊላክ ይቻላል፤ ወይም በምግብ ወይምማጠጥ ወስጥ ሊጨመር ይችላል። አባ ሰንጋ ከመኪና፣ ከሕንፃ ወይም ከአወሮፕላን ላይ ወደ አየር ሊረጭ ይችላል። የዚህ አይነቱ ጥቃት የአባ ሰንጋ ብናኞችን በቀላሉ በመርጨት በነፋስ ተገፍቶ ወይ በሰዎች ልብሶች፣ ጫማዎች እና ሌሎች ዕቃዎች ላይ መተላለፍን ያረጋግጣል። ብዙ ሕዝብን በአባ ሰንጋ ለማበከል የሚጠይቀዉ ጥቂት ማጠን ብቻ ነው። :

የአባ ሰንጋ ዘር ብናኞች ወደ አየር ከተለቀቁ፤ ሰዎች በትንፋሽ ወደ ወስጣቸዉ በማስገባት በአባ ሰንጋ ሊታመሙ ይችላሉ። የእስትንፋስ አባ ሰንጋ አይነት በአፋጣኝ ካልታከመ፤ በጣምአስከፊና በአጭር ጊዜ ሊገድል ይችላል። የበሽታዉ ጥቃት በ አሜሪካ ካሉ የመመርመርያ ማሪያዎች በአንዱ ካልተገኘ፤ ሐኪሞች ያልተለመዱ የበሽታ ሂደቶችን በድንገተኛ ክፍሎች ከሚመጡ ታማሚዎች ማየት እስኪጀምሩ ድረስ ላይታወቅ ይችላል።

**ለበለጠ መረጃ፤ www.cdc.gov/info ይጎብኙ**

**ወይምበ 1-800-232-4636 ይደውሉ**

ይህ ሰነድየተፃፈዉበአማርኛ ሲሆን፤ የእንግሊዝኛ ቅጂዉበ

http://www.cdc.gov/anthrax/basics/index.html ሊገኝ ይችላል፡

Fact Sheet - Amharic – 2016